# ያ ትውልድ

የ«ያ ትውልድ ተቋም» ልሳን

ያ ትውልድ ቅጽ 6 ቁጥር 2 ሰኞ የካቲት 11 ቀን 2011 ዓ.ም.

## የካቲት አብዮት፤ የታሪክ ትምህርት ቤት

*(ሰኞ የካቲት 11 ቀን 1966 ዓ.ም. ሕዝባዊ አብዮት 45ኛ ዓመት ምክንያት በማድረግ)*

በሀገራችን ሰኔና ሰኞ ይባላል፤ ዛሬ የካቲትና ሰኞ ብንል ወደ 45 ዓመት ትዝታ ይወስደናል። ልክ የዛሬ 45 ዓመት ሰኞ የካቲት 11 ቀን 1966 ዓ.ም. በኢትዮጵያ ከፍተኛው የለውጥ ሂደት የተቀጣጠለበት መነሻ ቀን ነበር።

የዛሬ 45 ዓመት ልክ በዛሬው ቀን የካቲት 11 ቀን 1966 ዓ.ም. የኢትዮጵያ መምህራን ማሕበር (ኢ.መማ) በቀዳሚው ሳምንት ባሳለፈው ውሳኔ መሠረት ያቀረባቸው ጥያቄዎች እስኪመለሱ የሥራ ማቆም አድማ ጠርቶ ነበር። የቀደሙት ሁለት ሳምንታት የትምህር ዓመቱ የመጀመሪያ ሴሚስተር ተገባዶ ት/ቤቶች ለገናና የጥምቀት በዓል የሚዘጉበት የዕረፍት ጊዜ ነበር። የመምህራን ማሕበሩ ያቀረባቸው ጥያቄዎች ከደሞዝና የሥራ ሁኔታዎች መሻሻል በተጨማሪ "ሴክተር ሪቪው" የተባለውንና በትምህርት ሚኒስቴር በሥራ ላይ ሊውል የነበረውን ዕቅድ በመቃወምም ነበር።

"ሴክተር ሪቪው" በመምህራን ብቻ ሳይሆን በወላጆችም ዘንድ ቅሬታን አስነስቶ ነበር። የ"ሴክተር ሪቪው" ዓላማ ያኔ ሕዝብ እንደተረዳው ተማሪዎችን ከአራተኛ ክፍል ጀምሮ "እያጣራ" አብዛኞቹን ወደ ሙያ ትምህርት ሲያሰማራ ጥቂቶች የአካዳሚክ ችሎታ አላቸው ተብለው የሚመረጡት ደግሞ ወደ ከፍተኛ የቀለም ትምህርት ማለትም ወደ ሕክምና፣ ምህንድስና፣ የሂሳብ፣ ሕግና ሌሎች የሳይንስ የትምህርት ዘርፎች የሚያሠማራ ነበር። መምህራንም ሆኑ ወላጆች ይህ አብዛኛውን የዝቅተኛውን መደብ ክፍል ልጆች አናፂ፣ መካኒክ፣ የቧንቧ፣ የኤሌክትሪክ፣ የሕንጻና መንገድ ሥራዎች ወዘተ. የሚያሠማራ አድሎአዊ የትምህርት ሥርዓት ነው በሚል በጥርጣሬና በተቃውሞም ነበር ያዩት።

በተለምዶው የዩኒቨርሲቲ፡ ኮሌጆችና የከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ተማሪዎች "ረብሻ" አንስተው ት/ቤቶችና ኮሌጆች ሲዘጉ ነበር የሚታወቀው። በዚህ የካቲት 11 ሰኞ ዕለት ግን መምህራን በኢትዮጵያ መምህራን ማሕበራቸው ውሳኔ መሠረት በሥራ ገበታቸው አልተገኙም ነበር። የዚያ ጊዜ ታዳጊ ሕፃናትና ወጣቶች ት/ቤት ተዘግቶ ወደ ዕረፍት በተለይ ወደ ሠፈር ጨወታ መመለሳቸው በወላጆችም ሆነ በሌላውም ህብረተሰብና በተማሪዎች በራሳቸውም ላይ ሁኔታው አዲስና ግር የሚል ስሜት አሳድሯል።

የየካቲት 11 ቀኑ የመምህራን ሥራ ማቆም መጀመር በሌሎችም የሕብረተስብ ክፍሎች ዘንድ "የዝምታ" ድጋፍ ነበረው። በተለይ ከጥቂት ሳምንታት በፊት በዛን ጊዜው ጠቅላይ ሚኒስትር በክቡር ፀሐፊ ትዕዛዝ አክሊሉ ሀብተወልድ ካቢኔ ውሳኔ በነዳጅ ዋጋ ላይ የተደረገው ጭማሪና ተያይዞም የስዊዝ ካናል መዘጋት ያስከተለው የኑሮ ውድነት ሕዝቡን አስከፍቶት ነበር። የሚገርመው የተደረገው ጭማሪ ለምሳሌ በአንድ ሊትር ቤንዚን ላይ 25 ሳንቲም ነበር። (የገንዘቡን የመግዛት አቅም ለማስታወስ ያህል ደርሶ መልስ የአንበሳ አውቶብስ ቲኬት አዲስ አበባ 25 ሳንቲም፣ በአምስት ሳንቲም አራት ደስታ ከረሜላ፡ በ 15 ሳንቲም ሻይ ቤቶች እንጀራ በሽሮ/ምሥር፣ ቢራ 50 ሳንቲም፡ ወዘተ ይሸመት ነበር)።

የመምህራን የሥራ ማቆም አድማ መደረጉ አዲስ ከስተት ከመሆኑ አለፈና ለሳምንት ዘለቀ ማለትም እስከ ዓርብ የካቲት 15 ቀን ድረስ። በውስጥ ለውስጥ የተደረጉ መምህራን ማሕበሩ የሥራ ማቆም አድማውን እንዲተው የማስፈራራት፣ የማግባባት ሙከራዎች ስለከሸፉ ቀዳማዊ ዓፄ ኃይለሥላሴ ራሳቸው በቴሌቭዥንና ሬዲዮ ቀርበው የተለመደውን "የሚወደንና የምንወደው ሕዝባችን . . . " በሚል ባስተላለፉት መልዕክት ሊተገበር ታቅዶ የነበረውን "ሴክተር ሪቪው" በመባል የሚታወቀውን አዲስ የትምህርት ፖሊሲ መነሳቱንና ጥያቄአቸውም እንደሚታይላቸው ገልጸው በሚቀጥለው ሰኞ የካቲት 18 ቀን መምህራን ወደ ሥራ ገበታቸው እንዲመለሱ "አሳሰቡ"። ተማሪዎችም፡ ወላጆችም መላው ሕዝብም የመምህራኑ ሥራ ማቆም ጉዳይ በዚህ ያለቀለት መሰለው። ንጉሱ በቴሌቪዥን መስኮት ቀርበው የተናገሩት አይደለም በአፈ ንጉሥ አማካይነት የሚያስተላልፉት መልዕክት እንኳ ማን ላይተገብር? ማን ደፍሮ ላያደምጥ?

ነገር ግን የሥራ ማቆም አድማው ከጀመረ ከሳምንት በኋላ ሰኞ የካቲት 18 ቀን ተማሪዎች በት/ቤቶች ቢገኙም አንድም አስተማሪ አልነበረም። መምህራን ከንጉሡ ነገሥቱም ማሳሰቢያ በኋላ በሥራ ማቆም አድማቸው መቀጠላቸው ሲሰማ ጭራሽ ያልታሰበና ያልጠበቀ ድንጋጤም ግራ መጋባትም ፈጠረ። ብዙ ወላጆች የትምህርት መቆም ሲያሳስባቸው እነርሱም ሆነ ሌላውም ሕዝብ ይህ ያልተለመደ የሥራ ማቆም ሁኔታ ያሰጋው ሳያንስ የንጉሠ ነገሥቱ ቀጥተኛ ትዕዛዝ አለመፈፀሙ የስጋቱን አድማስ አሰፋው። "ንጉሡ ተናቁ" የሚል አግራሞትና ተከትሎ ምን ይመጣ ይሆን? የሚለው ነገር የሁሉም መነጋገሪያ ሆነ።

ሆኖም አልቀረ በዚህ በተከታዩ ሳምንት ማለትም ከሰኞ የካቲት 18 በኋላ ያሉት ቀናትና ሳምንታት የሥራ ማቆም አድማዎች፣ የመብትና የኑሮ ውድነት መሻሻል ጥያቄዎች ወዘተ እንደ ማዕበል ይከታተሉ ጀመር። ከሁሉም በላይ የኢትዮጵያ ሠራተኞች ማህበር፣ የአዲስ አበባ ታክሲ ነጂዎች የሥራ ማቆም አድማውን መቀላቀል ሀገሪቱን በተለይ አዲስ አበባን ቀጥ ከማድረግ አልፎ ይህ ሕዝባዊ ማዕበል የማይቆም መሆኑን አመልካች ነበር። የመለዮ ለባሹ የዚህ ሕዝባዊ ንቅስቃሴ ተሳታፊ መሆን የጠቅላይ ሚኒስትር አክሊሉ ሀብተወልድ ሙሉ ካቢኔ ከሥራ መልቀቅ ጋር ሲደመር ጉዳዩ ከተቃውሞ፣ የመብትና የደሞዝ እንስቃሴ ከመሆን አልፎ ጥልቀት፣ ስፋትና ጥንካሬ እየጨመረ የሥርዓት ለውጥ የሚያመጣ አብዮት መሆኑ ግልፅ እየሆነ መጣ።

ይህ ሰኞ የካቲት 11 ቀን 1966 ዓ.ም. በመምህራን ሥራ ማቆም የተለኮሰው አብዮት ንጉሠ ነገስታዊውን የፊውዳል ሥርዓት እንገጫግጮ ከሥረ መሠረቱ ነቅሎ አዲስ ሕዝባዊ ዴሞክራሲያዊ መንግሥትና የተጀመረውን አብዮት ከዳር የሚያደርስ፡ ለዚህም የተነሱትን የመብት፣ የመሬት ይዞታ፣ የሃይማኖቶች የብሔሮች ዕኩልነት ወዘተ. የሚመልስና መፍትሔ የሚሆን መንግሥታዊ አስተዳደር

የመዘርጋት ንቅናቄው 5 ወራት ባነሰ ጊዜ ወስጥ ሰኔ 21 ቀን 1966 ዓ.ም. የተቋቋመው ወታደራዊው ደርግ ጠልፎ ወሰደው። በ3 ወር ጊዜ ውስጥም ኀሙስ መከረም 2 ቀን 1967 ዓ.ም. ንጉሡ ነገስቱን ከሥልጣን አውርዶ ራሱን "ጊዚያዊ ወታደራዊ አስተዳደር ደርግ" ብሎ ሥልጣን ያዘ።

የካቲት እንቅስቃሴ "ሕዝባዊ አብዮት" የሚባለው ለፈጠራ ወይም የወቅቱን እቅስቃሴ ያልነበረ መልክ ለመስጠት አይደለም። ለየካቲት አብዮት ዋናው ምክንያት በጊዜው የነበረው ሥርዓት ንጉሣዊ ቤተሰብን፣ መኳንንትና ባላባቱን ብቻ ፈላጭ ቆራጭ አድርጎና አጉልቶ ሌላውን በማፈን፣ በመበዝበዝ፣ በማስራብ፣ በማደህየት፣ "የምንወደውና የሚወደን ሕዝባችን" ከወሬ ያልዘለለ መደለያ መሆኑ ነው።

የኢትዮጵያ መምህራን የትግል ታሪክ በአግባቡ ባይዘገብም ትልቅ አስተዋጽዖ እንደነበራቸው የካቲትና የደርግ ዘመን ምሥክሮች ናቸው። የኢትዮጵያ መምህራን በጊዜው በነበረው የኢትዮጵያ መምህራን ማህበር (ኢ.መማ) ለመብታቸው ተሟግተዋል። ተማሪውን በማነሳሳት መምህራን ተማሪዎቻቸውን በዕውቀት ከማነጽ ባሻገር በፖለቲካው፣ በኢኮኖሚው፣ በማህበረሰብ ተማሪውን በመቀስቀስ፣ በማነሳሳት አኩሪ እንቅስቃሴ እንደነበራቸው ይታወቃል። በዘመነ ደርግም ሆነ በኢሕአዴግ አገዛዝ ያደረጉትና የሚያደርጉት ፖለቲካዊ እንቅስቃሴ ብቻ ሳይሆን ለሀገራቸውና ለሕዝባቸው የከፈሉት የአካልና የሕይወት መስዋዕትነት ቀላል አይደለም። የካቲት 66 ሲነሳ የነበራቸው ቁልፍ ሚና ብቻ ሳይሆን አንቀሳቃሽ ሞተር በመሆናቸው የጎላ ሥፍራ አላቸው።

በወቅቱ በተለይ በአዲስ አበባ በአሁኑ ወቅት በመላው ሀገሪቷ የሚንቀሳቀሱ የታክሲ ሹፌሮች ከህብረተሰቡ ጋር እጅግ የተቆራኘ ግንኙነት ስላላቸው የኅብረተሰቡን ኑሮ፣ ብሶት ለማድመጥና ለመቃኘት ያላቸው ዕድል የላቀ ነው። በሚደረጉም ሕዝባዊ ትግሎች የሚያበረክቱት ድርሻ ቀላል አይደለም። ለራሳሸው መብትም ሆነ ተገን አድርገው ለህብረተሰቡ በመቆርቆር የሚያደርጉት ትግል በአብዛኛው በሥራ ማቆም የታጀበ ነው። ይህ ታድያ የከተሞችን እንቅስቃሴ እጅጉን ይገታል፣ በተዘዋዋሪ በሠራተኛውና በህብረተሰቡ የቀን ተቀን እንቅስቃሴ መቋረጥ ላይ ከፍተኛ ድርሻ ስላላቸው መንግሥትን ወጥረው ከሚይዙና ከሚያሽመደምዱ ክፍሎች ዋነኛውን ሥፍራ ይይዛሉ ቢባል ማጋነን አይደለም። የካቲት 66 ሲወሳ የታክሲ ሹፌሮችና አስተዋጽዖአቸው ሁሌም ቅድሚያ ይሰጠዋል። በዚህም ሕዝባዊ ወገንተኝነታቸውና ለከፈሉት መስዋዕትነት ታሪክ ሲያስታውሳቸው ይኖራል።

ለየካቲት እንቅስቃሴ ተማሪዎች ከፍተኛ አስተዋጽዖ አድርገዋል እንጂ በሀገርና ሕዝብ ላይ ያመጡት "ጣጣ" አይደለም። ተማሪዎችና የዘመኑ ተራማጅ ኃይሎች በወቅቱ የነበረውን የኢትዮጵያን ሕዝብ መሠረታዊ ጥያቄ በማንገብ ግምባር ቀደም በመሆን አስተጋብተዋል። ተማሪዎች በኅብረተሰቡ ውስጥ ያሉ ዋልታ ኃይል ናቸውና የቤታቸውን፣ የአካባቢአቸውን፣ የቀዬአችውን ብሶትና መከራ በከተማም በገጠርም አድገውበት በመምጣታቸው ጥያቄአቸው የሕዝብ እንጂ የነሱ አይደለም። በተለይ በጊዜው በነበረው የቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ዩንቨርስቲ ምንም እንኳ ተቃውሞው ከውስጣዊ የዩንቨርስቲው አስተዳደራዊ ሂደት መነሻ አድርጎ ቢንቀሳቀስም፤ እነዚህ አስተዳደራዊ ጥያቄዎች የሚያስከትሉት እሥርና እንግልት ጉዳዩ ያለው ሥርዓቱ ላይ እንዲሆን ግንዛቤ እንዲያገኙ እረደቷቸዋል። ሲያያዝም ሰፋ አድርገው የኢትዮጵያን ገበሬ ሕይወት፣ የሠራተኛውን ስቃይ፣ የኅብረተሰቡን ብሶት ሲቃኙ፣ የሀገሪታን ኋላ ቀርነት ሲመለከቱ የችግሩ ቁኝጮ ሥርዓቱና አገዛዙ በመሆኑ ተጋፍጠው ታግለዋል። በምላሹም እሥር፣ እንግልት፣ መስዋዕትነት ቢከፍሉም ትግሉን ጥንካሬ እየሰጠው፣ እንቅስቃሴው ሕዝብ ጆሮ እየገባ፣ ፋና ወጊ ሁነው የጀመሩት ትግል ሕዝባዊ መልክ ይኖረው ዘንድ ያበረከቱት

ታሪካዊ ተጋድሎ ሊያስወቅሳቸው አይገባም። ተማሪዎች ለመሬት ለአራሹ፣ ለዴሞክራሲ መብት፣ ለሕዝባዊ መንግሥት፣ ለድሀ መማር፣ ለኑሮ መሻሻል ታገሉ እንጂ ደርግ ይምጣልኝ ብለው አልጮኹም። ተማሪዎችና የወቅቱ ተራማጅ ኃይሎች ታግለውና ተደራጅተው ሕዝብን ማቀፍ ሳይችሉ የየካቲት አብዮት የዛሬ 45 ዓመት በዕለተ ሰኞ ቀደማቸውና አብዮቱን ለመሸከም አቅም አልነበራቸውምና እንጋጠው እያዩት የካቲት በረረባቸው። የየካቲት 66 አብዮት ሲወሳ የኢትዮጵያ ተማሪዎች እንቅስቃሴ ጉልህ ሥፍራ ይሰጠዋል። የከፈሉት እንግልትና መስዋዕትነት ሲታሰብ ይኖራል። ለዛሬም ወጣቶችና የተማሪዎች እንቅስቃሴ ቀደምት የትግል ታሪካቸው አስተማሪ ነው።

ከጥንታዊ ባለ ታሪክ ሀገርነቷ ኢትዮጵያን የት ሊያደርሳት የሚችል ዘመን ቢኖር የዓፄ ኃይለሥላሴ ዘመን ነበር። ከእምነቱና ከባህሉ የተነሳ አሜን ብሎና ሰግዶ የተገዛላቸውን ሕዝብ ባይራብ፣ በሕክምና እጦት ባይሰቃይ፣ በድንቁርና ባይከበብ፣ በየሀገረ ገዢው ባይንገላታ፣ ለተመጣጣኝ ኑሮው ተመጣጣኝ ክፍያ ቢደረግለት፣ የመሬትን ስሪት ቢያሻሽሉ፣ ሀገሪቷን ወደ ዕደገትና ስልጣኔ የሚወስድ አቅጣጫ ቢተልሙ በንጉሡ ላይም ሆነ በሥርዓቱ የሚወዱት ሕዝባቸው ባላመጸ። ግፉን መሸከም ሲሳነው “ንጉሥ አይከሰስ ሰማይ አይታረስ”ን ዘንግቶ መከሰስ አይደለም መደርመስ እንደሚችል ሆኖ ለመብቱ በየአቅጣጫው ሕዝባዊ ቁጣ በመነሳቱ ነው ሕዝባዊ አብዮት የሚባለው።

ሰኞ የካቲት 11 ቀን 1966 ዓ.ም. የጀመረው የመምህራን የሥራ ማቆም አድማ ለሳምንት ያህል ሲዘልቅ በቀጣይነት በታክሲ አሽከርካሪዎች ታጀበ። እስላምና ክርስቲያኑ “የሃይማኖት አድሎ ያብቃ” ሲሉ በጋራ አደባባይ ወጡ። የጦር ሠራዊቱ የደሞዝ ጭማሪ ወዲያውኑ አቀረበ። ሠራተኞች፣ ትምህርት ቤቶች የእንቅስቃሴው ተካፋይ ሆኑ። አማራጭ ያጡት የንጉሡ ዋልታ ክቡር ጠቅላይ ሚኒስትር ፀሐፊ ተዕዛዝ አክሊሉ ሀብተወልድ በፈቃዳቸው ሥልጣናቸውን ለቀቁ፤ ካቢኔአቸውን በተኑ። ክቡር እንዳልካቸው መኮንን በጠቅላይ ሚንስትርነት ተሾሙ።

ወደ ሃምሳ ዓመት በሚጠጋው የዓፄነት አገዛዛቸው ታማኝና አገልጋይ ወታደራዊ ኃይላቸው ሳይቀር እየከዳቸው ወገንተኝነታቸውን ከሕዝብ አደረጉ። እንቅስቃሴው እየተጠናከረና እየገፋ መጣ። በተማሪውና በተራማጁ ክፍል ከዓመታት በፊት ሲውጠነጠንና አደባባይ ብቅ ብሎ ማታገያ መፈክር የነበረው “መሬት ለአራሹ” እጅጉን ተውለበለበ። ለአዲሱ የጠቅላይ ሚኒስትር እንዳልካቸው መኮንን ሹመት “ጉልቻ ቢለዋወጥ ወጥ አያጣፍጥም” በሚል ርዕስ የሥርዓት ለውጥ ጠያቂ በራሪ ወረቀት በተለይ በአዲስ አበባ ከተማ በከፍተኛ ደረጃ ተሰራጨ። እንቅስቃሴው አድማሱን አስፍቶ ለ50 ዓመት ሀገሪቷን የገዙት ዓፄ ኃይለሥላሴ ብቻ ሳይሆኑ ሲወርድ ሲዋረድ ለሺህ ዘመናት የኖረውን ዘውዳዊ ሥርዓት ደረመሰው። የካቲት አብዮት የአንድ አገዛዝን የሥርዓት ለውጥ ብቻ ሳይሆን እየተወራረሰ በተከታታይነት የመጣውን ዘውዳዊ አገዛዝ የገረሰሰ በመሆኑ ነው የአብዮቱ ሥርነቀልነት።

የካቲት ቃላት ወለደ፤ ከተቀጽላ አጠራሩ አብዮት ጀምሮ አድሃሪ፣ በዝባዥ፣ አቆርቋዥ፣ ፊውዳል፣ ቡርዣ፣ የመሳሰሉት ህብረተሰቡ ዘንድ ሰርፀው እንዲገቡ በመዝሙሮች ሁሉ ታጀቡ። አብዮቱ አቅጣጫውን ሊስት ሲንደረደርም ይወድማሉ፣ ይደመሰሳሉ፣ እናቸ(ሸ)ንፋለን፣ ላብ አደር/ወዝ አደር፣ አድርባይ፣ ባንዳ ወዘተ የግዜው ተራማጆች ቋንቋዎች ሆኑ።

የካቲት አብዮት ወለደ እንጂ ማን ያሳድገው የሚለውን ምላሽ አልነበረውም። የካቲት የሕዝብን ጥያቄ በተለይ የመሬት ለአራሹ፣ የዴሞክራሲ መብት፣ የሕዝብ መንግስት፣ ለአደባባይ ሲያወጣ ምላሽ የሚሰጠውን አላዘጋጀም ነበር። የካቲት አብዮት ያልፈለገውን የዓፄ ሥርዓት የማስወገድ አቅሙ ጠንካራ ቢሆንም የሚተካውን ግና አላዘጋጀም። መልዕቋ እንደጠፋ መርከብ የሚወዛወዘው የየካቲት አብዮት አቅጣጫውን መሳት ብቻ ሳይሆን የሚይዘውም ግራ በተጋባበት ሁኔታ በእንቅስቃሴው ወቅት

ለትግሉ የእንቅስቃሴው አካል የነበረው ወታደሩ ክፍል "ታሪክ የጣለብን አደራ" በሚል ከሠራዊቱ የተውጣጣ ቡድን ተመሠረተ። ከጦር ኃይሎች፣ ከፖሊስ ሠራዊት፣ ከክብር ዘበኛ የተውጣጣው አስተባባሪ ኮሚቴ ***"በኢትዮጵያ ትቅደም"*** መፈክር ብቅ አለ። ወዲያውኑ ሥልጣን ባይያዝም የንጉሡን መዋቅር በመቆጣጠርና እራሱን በማደራጀት ያለምንም ተቃውሞ የንጉሡን የቀድሞ ባለሥልጣናት በቁጥጥር ሥር በማድረግ ከቤተ መንግሥት፣ ከቤተ ድሎት ወደ እሥር ይከታቸው ጀመር። የአብዮቱን ሰላማዊነት ለማድመቅም ***"ያለምንም ደም፤ ኢትዮጵያ ትቅደም"*** በተደጋጋሚና በማያቋርጥ ፍጥነት ከሕዝብ ጆሮ ይደርስ ጀመር።

ይህ አስተባባሪ ኮሚቴ በስልትና በዘዴ እየተጓዘ ሰኔ 21 ቀን 1966 ዓ.ም. እራሱን "ደርግ" ብሎ ሰየመ። አዲሱን ጠቅላይ ሚኒስትር እንዳልካቸው መኮንን ሳይቀር ወደ ሥር አስገባ። ልጅ ሚኬል እምሩ ተተኪ ጠቅላይ ሚኒስትር ሆኑ። ደርጉ ጥንካሬውን ለማጎልበትና መንግስታዊ መዋቅሮችን ለመቆጣጠር ንዑስ የደርግ አባላትን ማስፋፋት ሲያደርግ በሌላ በኩል በሥርዓቱ ተጠያቂ ናቸው የተባሉ ባለሥልጣናት ባላባትና መኳንንት የጦር ሹማምንት ወደ እሥር መከተት የቀን ተቀን እንቅስቃሴ ሆነ። ይህን "ሰላማዊ" ለውጥ ባለመቀበል እጃችንን አንሰጥም ላሉትም ***"የፍየል ወጠጤ ትክሻው ያበጠ ልቡ ያበጠበት. . ."*** ከወታደራዊ ማርሽ ጋር "ተረሸኑ፣ ተደመሰሱ" በሚሉ ቃላት ሞትን ያበሥር ጀመር።

ሰኞ የየካቲት11 ቀን 1966 ዓ.ም. እንቅስቃሴን 45ኛ ዓመት ስናስታውስና ዛሬ ላይ ሁነን ሀገራችን የት ናት? ምን አተረፍን? ምን አገኘን? ስንል "ትሻልን ትቼ ትብስን አገኘሁ፤ ቀጥዬም ብታገል ትባባስን አየሁ" በሚል ብቻ የሚተው አይደለም። በሕዝብና በሀገር ላይ የሚፈፀም ብሶትና ግፍ ሲበዛ ሕዝባዊ ዐመጽ ሊከሰት እንደሚችል የካቲት ያስተምረናል። ከዘመነ መሳፍንት ባሻገር ለሺህ ዘመን የኢትዮጵያን አንድነት ጠብቆ የኖረው ዘውዳዊ አገዛዝ መገርሰሱ የሥርዓት ለውጥ ብቻውን መሠረታዊ የሀገርና የሕዝብ ጥያቄዎችን እንደማይፈታ የካቲት አብዮት ትምህርት ይሆናል። በሀገርና በሕዝብ ንብረትና በሌላም ተጠያቂ ናቸው የተባሉ የወደቀውን ሥርዓት ባለሥልጣናት ማሰር/መግደል የሕዝብና የሀገርን ጥያቄ ለመመለስ ቁልፍ እንዳልሆነ የካቲት ያስተምረናል። በሕዝባዊ መሠረት ላይ የተገነባ ድርጅታዊ አካል እጦት ሕዝባዊ እንቅስቃሴ አሸናፊነቱ ያለውን አገዛዝ ለመጣል እንጂ ሕዝባዊና ሀገራዊ ጥያቄዎችን ላይመልስ እንደሚችል ልማር ላለ የዛሬ 45 ዓመትን ታሪክ ይቃኝ። የካቲት 66 አብዮት ሊማሩበት የሚገባ፣ ከታሪክ ማህደር የማይፋቅ፤ ለኢትዮጵያ ብቻ ሳይሆን ለነፃነት ታጋዮች "የከሸፈ አብዮት" ተምሳሌት ነው።

የካቲት አብዮት ተማሪ ያመጣው ጣጣ ተብሎ ታሪክ ሚዛባበት አይደለም። ተማሪ ደርግ ይምጣልኝ ብሎ አልታገለም። ተማሪ ለገዳይና ጨፍጫፊ ፋሺስት መንግሥቱ ኃይለማርያም አልታገለም። እንደውም ገና ከጅምሩ ደርግ በሞግዚት አስተዳደር ስም ዓፄ ኃይለሥላሴን አስወግዶ በትረ መንግስቱን በጊዜያዊ አስተዳደር ስም ሲይዝ ከሁሉም የተውጣጣ መንግሥት ብሎ ***"ጊዜያዊ ሕዝባዊ መንግሥት"*** ካለው ኢሕአፓ ጋር ትግሉን ተቀላቀለ እንጂ። ተማሪ ጩኸቱ ለሕዝብ ጥያቄ ምላሽ ነበርና ገና ከጅምሩ የመሰብሰብ፣ የመደራጀት፣ የመፃፍ፣ የመናገር መብት ደርግ ሲያፍን ***"የዴሞክራሲ መብት ያለገደብ"*** ተሸካሚ ሆነ እንጂ አፈናው ይቀጥል ብሎ ደርግን አላቀፈም። ደርግ የካቲት አብዮትን አቅጣጫ አስቶና ገና ከጅምሩ በጅምላ 60ዎቹን ሲረሽን ***"ጭፍን ፋሺዝም በኢትዮጵያ ነገሠ"*** ያለውን እናት ድርጅቱን ኢሕአፓ ተቀላቅሎ መታገሉ እውን ወንጀል ነውን? "ቀናተኛ ነኝና እኔ ብቻ ልግዛ" ያለው ደርግ ለሚቃወመው ምላሹ ጥይት ነውና "በቀይ ሽብር" ስም ለየካቲት አብዮት ዋልታ የነበረውን ተማሪና ትውልድ ለመጨረሱ የካቲት አብዮት ሳይሆን የደርግ አገዛዝ ያመጣው ለመሆኑ "ሃቅ አያንቅ" ካልሆነ በቀር ታሪክ ማገላበጡ በቂ ነው።

የወሎ ረሃብን በዓይኑ ያየ የዚያ ትውልድ አካል ለሥርዓቱ መገርሰስ ሆ! ብሎ ቢነሳ አያስደንቅም። በጊዜው በ10 እና 20 ሺህ ጋሻ መሬት ባለቤትነት ገበሬውን እንደ ሀብታቸው፣ አገልጋያቸው ቀፍድደውና አደንቁረው የያዙትን ጥቂት ባላባቶች ያየ ስለ ፍትህና የሥርዓት ለውጥ ቢያቀነቅን ***"አትነሳም ወይ! አትነሳም ወይ! የግፍ አገዛዝ አይበቃህም ወይ! ተነስ! ተነስ!"*** እያለ በየአደባባዩ ቢቀጠቀጥ አያስገርምም። በጊዜው ባለው የኑሮ ደረጃ ሕክምና የማያገኘውን ዜጋ፣ መማር ያቃታቸውን ሕፃናት ያስተዋለ፣ ይባስ ብሎ በአዲስ የትምህርት ፖሊሲ ከአገዛዙ ባለሥልጣንና ከጊዜው ሀብታሞች በቀር የልጆች የትምህርት ደረጃን ገድቦ የሚያስቀር ፖሊሲ አደገኝነቱን የተረዳ ትውልድ ***"ደሀ ደሀ ደሀ ምን ታየበት፤ እንዳይማር የሆነበት"*** እያለ ቢዘምር አያስደንቅም። የቁጥር ማነስ አይደለምና የእንቅስቃሴው አካላት ሲታፈኑ፣ ሲታሠሩ፣ ሲገደሉ፣ ያየ ትውልድ ***"ነፃነት ነፃነት የምትሹ፣ ታገሉለት አትሽሹ"*** ብሎ መዘመሩ አግባብ አይደለምን? በዓፄ ኃይለሥላሴም ዘመን፣ በደርግ አገዛዝ፣ አሁን በአለው የኢሕአዴግ 27 ዓመት ሰቆቃ ተማሪዎችና ወጣት ትውልዶች ለሕዝብ ስለሕዝብ ጮኹ፣ ስለ ሀገራቸው ታሰሩ፣ ተደበደቡ፣ ተገደሉ፣ ተሰደዱ ቢባል ሚዛን ይደፋል። ይህን ስንመለከት አሁንም ለሀገራችን የግዛት ሉዓላዊነት፣ ለሕዝባችን አንድነት ጨምሮ ለዴሞክራሲያና ለዜግነት መብት ተግባራዊነት፣ ለሕዝብ መንግሥት አስተዳደርነት፣ ጨምሮ የካቲት 66 ላነሳቸውና ዛሬም ምላሽ ላላገኙት ሀገራዊና ሕዝባዊ ጥያቄዎች ወጣቶችና የዛሬው ትውልድ ኃላፊነት አለባቸውና አቅጣጫውን ከሳተው የ45 ዓመቱ የካቲት አብዮት ትምህርት በመቅሰም ተደራጅተውና አደራጅተው መንቀሳቀስ እንደሚኖርባቸው ሊገነዘቡ ይገባል።

በኢትዮጵያ በተከሰተው የየካቲት 66 እቅስቃሴና እስከዛሬም በሚደረጉ ትግሎች የአንዳንድ ባዕዳን ኃይሎች በተለይ የአረቡ ዓለም ሚና ከቶውንም ሊዘነጋ አይገባም። የውስጥ ችግር ቢኖርባትም ነፃነቷን ጠብቃ የኖረችው አፍሪካዊት ሀገር ኢትዮጵያ በዲፕሎማሲው መስክ፣ በተባበሩት መስግሥታት መሥራች አባልነቷ፣ ቀዳሚ የዓለም ሰብዓዊ መብት ሠነድ ፈራሚነቷ፣ የአፍሪካ አንድነት ድርጅት መሥራችነቷ ስሟ ከፍ እያለ መምጣቱ ያሳሰባቸው ባዕዳን ኃይሎች በተለይ የአረቡ ዓለም ሚና ቀላል አልነበረም። ኢትዮጵያን ለማዳከምና ለመበታተን ካላቸው የቆየ ዕቅድ በ1960ዎቹ መንቀሳቀስ የጀመሩ የፖለቲካ ድርጅቶችን በከፍተኛ ደረጃ በመርዳት ኢትዮጵያ እንድትበታተንና በቁጥጥራቸው ሥር ለማስገባት ያደረጉት ሤራ ዛሬም ያልቀዘቀዘ መሆኑ እየታየ ነው። ሻቢያ፣ ጀብሃ፣ ህወሓት፣ ኦነግ፣ ኦብነግ፣ ምዕራብ ሱማሌ ነፃ አውጭ ግምባር እና ሌሎችም ድርጅቶችን በገንዘብና በቁሳቁስ እርዳታቸው ከበስተጀርባ ያግዙ እንደነበር አይዘነጋም። ኢሕአፓም ወደ ኋላ በኢትዮጵያዊነቱ እጅጉን ያከረረ አቋም እየያዘ መምጣቱ ሊገፉበት ባይችሉም የአረቡ ዓለም ድጋፍ ተቋዳሽ እንደነበር ይታወቃል። የኢትዮጵያ ሕዝብ በአለበት ችግርና መከራ በመጠቀም እውነተኛ ለውጥ ፈላጊና፣ ለሀገሩ ተቆርቋሪ ትውልድ ላይ ያለ ኃይላቸውንና ገንዘባቸውን አፍስሰው በብሔር/ብሔረሰቦች መብት ስም ኤርትራን አስገንጥለዋል። አሁንም ያልበረደ የመበታተን አደጋ ይኖር ዘንድ በአደራጁት ህወሓት ተባባሪነት ሀገሪቷን በዘርና ቋንቋ ክልል በመከፋፈልና የመገንጠል መብት በሠጠ ሕገ መንግሥቱ ዛሬም ክልሌ ብቻ ባይ ዜማ ሲሰማ መደመጡ የየካቲት 66ቱ አብዮት አስተዋጽዖ እንደነበር ሊካድ አይገባውም። በለውጥ ስም በአለብን ቁስልና ደካማ ጎን በመጠቀም የውጭ ኃይሎች ድጋፍ የሰጡ እየመሰለ እንዴት አድርገው እርስ በርሳችን እየከፋፈሉ ዛሬ ለደረስንበት አደገኛ ሀገራዊ ሁኔታ እንዳደረሱን የካቲትና አብዮቱን በመመርመር ትምህርት ሊወሰድበት ይገባል።

በመጨረሻም ***"ያ ትውልድ ተቋም"*** የካቲት 1966 ዓ.ም. 45ኛ ዓመት ምክንያት በማድረግ ከተቋቋምንበት ጊዜ አንስቶ ለስድስተኛ ጊዜ ብዕራችንን ስናነሳ በትግሉ የተሰዉ ወገኖቻችንን እየዘከርን፣ ቤተሰቦቻቸውን እያሰብን፣ የአካልና የስነ ልቦና ሰለባ የሆኑትን እያጽናናን እንደሚሆን

እንገልፃለን። የካቲት አብዮት ለትውልድ የሚተላለፍ አስተማሪ የታሪክ ሀብት ነው። የተከፈለው መስዋዕትነት ሕዝባዊ ድልን ባያስጨብጥም የየካቲት አብዮትን የምናጥላላውና አንቋሸን የምናየው ሳይሆን፤ ሀገር የሕዝብና የልጆቿ እንድትሆን፣ የኢትዮጵያ የግዛት አንድነት እንዲጠበቅ፣ ልጆቿ በዘር ተከፋፍለው ሳይሆን በኢትዮጵያዊነት ስሜታቸው እንዲተቃቀፉ፣ ያልተገደበ መብት ለሀገርና ለሕዝብ እንዲሆን፣ ሕዝባዊ መሠረት ያለው አገዛዝ በሕዝብ ፈቃድና አግባብ ባለው ምርጫ ተግባራዊ ይሆን ዘንድ፣ ለሴቶች መብት የሞገተ፣ ከነስህተቱ "ለብሔር/ብሔረሰቦች መብት" የጮኸ፣ እስላምና ክርስቲያኑን በጋራ ያሰለፈው የካቲት አብዮት አስተማሪ ነውና ታሪኩን ሁሌም እናነሳለን።

ከየካቲት 66 አብዮት መማር ለትግል መሠረት ነው!!!
የያ ትውልድ ታሪክ ህያው ነው!!!

የካቲት 11 ቀን 2011 ዓ.ም. (February 18, 2019)

«ያ ትውልድ ተቋም» ለመረጃ ምንጭነት!
የተጐዱ ወገኖችን ለመርዳት!
ለያ ትውልድ መታሰቢያነት!

«ያ ትውልድ ተቋም»

- ኢሜል : yatewlid@gmail.com,
- ድረ ገጽ : http://www.yatewlid.com, http://www.yatewlid.org, www.redterror.org, www.thatgeneration.org
- ምስለ ገጽ : yatewlid